# የኢትዮጵ ብሔራዊ የስደት መንግስት

## Ethiopian National Government In Exile

Mailing Address: 2901W Parker Road #864631 Plano, Texas
Email: yehar9@aol.com, Phone Number: 214-642-0394

Dallas, Texas
December 20, 2018

ይድረስ ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ
አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ አፍሪካ።

መጀመርያ የከበረ የኢትዮጵያዊነት ሰላምታችን ይድረሰዎ።

የደብዳቤያችን አላማ የብሄር ክልል እና የክልል መንግስት ይፍረስ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ፡ በቅድሚያ ወደ ዋናው ደብዳቤያችን ከመግብታችን በፊት ፡እንዲገነዘቡልን የምንጠይቀዎ ፡ የደብዳቤያችን አላማ ብለን ያስቀመጥነውን መታገያ አድርገን የተነሳነው እና የጀመርነው ቀድም ሲል መሆኑን እና ዛሬ እርሶ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆንዎት ሳይሆን ፡ በጥቅሉ 31 አመት ያስቆጠረ ብዙ መስዋእትነትን በልጅነት እድሜያችን በሃያው ውስጥ ከ1986 እ.አ.አ. ጀምሮ ይዘን ስንታገልበት እስከዛሬም የቆየንበት ለመሆናችን ነው። ይሄም አላማችን ድርጅታችንን ብቸኛው እና ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ ትልቁ እና ዋነኛው ፕሮግራሙ መሆኑ ነው። ይህ ውሳኔያችን ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን መከራ ከመተከሉ በፊት እና
ከተተከለም በሁላ ከስሩ እንዲነቀል በማሰብ ነው። ለመረዳት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሊንክ ይመልከቱ
http://dfwethiopiancommunity.blogspot.com/2014/03/ethiopian-national-government-in-exile.html"

የደብዳቤያችን ዋና መነሻ በህዳር 18 ቀን ፡ 2011 (ኖቨምበር 27) ሁሉንም የተቃዋሚ ድርጅቶችን ያላካተተ ፡ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶችን ኢሃዴግ በእርሶ አማካኝነት ጠርቶ ያደረገው ስብሰባ ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት ያቀረበውን የስደቱን መንግስት ፕሮግራም እና አጀንዳ ጠልፎ (hijack) መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም ሌላ ማብራሪያ ባጭሩ ለማቅረብ ሁኔታው አስገዶናል። እኛን ወደ ጎን ተቶ ኢሃዴግ ስብሰባ ከመጥራት ይልቅ ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስቱ እንደ ጀመረው ቢያዘጋጀው ኖሮ ማለትም እርሶን እና ድርጅትዎን ኢሃደግን አካተን ፡ ባጭር ጊዜ ውስጥ ፡ ምንም መፈራረት እና መደባበቅ የሌለበት ለሕዝቡም በግልጽ የሚቀርብ ትልቅ ለውጥ ለአንዲት ኢትዮጵያ ለአንድ ሰንደቅ ዓላማ እና ለአንድ ሕዝቧ ነጻነት አጎናጻፊ የሆነ ዴሞክራሲ ለመጀመሪያ እና ለመጨረሻ ጊዜ በሕግ የበላይነት የሚሰራ ፡ ሕዝባዊ ሕገ መንግስት በጋራ ስምምነት በነደፍን ነበር።

በድርጅትዎ ስብሰባ ላይ ሲናገሩ ፡ የሴት አይምሮ ከወንዱ በተለይ አርቆ ስለማሰብ እና በፍጥነት መፍትሄም በማግኘትም የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው ብለው ነበር። በሚገባ አስቀምጠዋል ሃቁን ልክ ነው። እዚህ ላይ ልናስገነዝብ የፈለግነው እና እንዲሰመርበት የምንጠይቀው ፡ ኢሃዴግ ያቀረበው ፕሮግራም (program) አጀንዳ እና ስብሰባ ፡ እንዳለ ከሴት አይምሮ የፈለቀ እና የተነደፈ እንጂ ፡ ከኢሃዴግ ወይም ከተቃዋሚዎቹ (ወንዶች ) የፓለቲካ ፓርቲ መሪዎች ነን ከሚሉት የፈለቀ እንዳልሆነ ነው። ሃቁ አንዱም የፓልከቲካ ፓርቲ መሪ ፕሮግራም ይዞ የገባም የለም። ለዚ ነው እርሶ ፕሮግራማችሁን እየጻፋችሁ በግል አቅርቡ ብለው መመሪያ የሰጥዋቸው። እኛ በመስከርም 15 ቀን በ1986 እ.አ.አ. የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላም እና ለዴሞክራሲ ፓለቲካል ድርጅትን ስናቋቁም በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት: ወንዶቹን አነሳስተን መልምልን በድርጅታችን ውስጥ ያለጾታ ልዩነት አሰለፍናቸው። ይህ ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል። በአገር ቤትም ይሁን በውጪው አለም አሜሪካን አገር ጭምር እኛ የፓለቲካ ፓርቲ በ1986 ስናቋቁም ወንዱ እንደእኛው መቋቋም ሙብቱ

ቢሆንም ገና በሃሳቡ አልታየውም ነበር። የበኩላችንን ወትውተናል ለምነናል ነገር ግን መንግስቱ ኃይለማሪያም ከስልጣን ሲወርድ ብቻ ነው አገር ገንጣዮችን የምንታገለው ነበር ያሉን። ከዛም ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ከስልጣን ሲወርዱ በ1991 እ.አ.አ. ጆርጅ ኤች ድብልዩ ቡሽ ቤተመንግስት ወያኔን በሄርማን ኮሀንን አማካኝነት ካስገቡ በኋላ ወንድሞቻችን እና አባቶቻችን እንዳሉት የፓለቲካ ፓርቲ በማቋቋም በትግሉ ተቀላቀሉ ማለትም የእየራሳቸውን ድርጅት ይዘው። እኛም እነሱ እኅናቸው ቆመን ሁሉንም በማስተባበር ማገዝ ጀመረን በተለይም በዲፕሎማሲው ግንኙነት ትልቅ እገዛ እናደርግ ነበር። እንደሴቶቹ ቢሆን ኖሩ ቀደም ብሎ ወያኔ ቤተመንግስት እንዳይገባ መታገሉ በቀደመ ነበር። አዎ ሴቶች አርቀው የማሰብ ችሎታ አላቸው የሚልው በሳይንስ የተጠና ሲሆን በእኛም በኩል በተግባር እናውቀዋለን ለማለት ነው።

ከዚች ደብዳቤ ጋር ለማስታወስ ያህል ይረዳ ዘንድ ፡ በቀጥታ ለእርሶ የተጻፉትን ደብዳቤዎች ማለትም ወደ አዲስ አበባ የተላከውን እና በኢትዮጵያ ኤምባሲ በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው በአምባሳደሩ በኩል የተላከውን ፡ በተጨማሪ ከአሜሪካን መንግስት ጋር የተደረገውን ስብሰባ የሚያሳይ ፡ ከሄርማን ኮሀን የተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ ፡ አውስትራሊያ በሚገኘው በኤስቢኤስ ሬድዮ በተለይ ኖቭምበር 12 ያደረግነውን ቃለምልልስ (ኢሃዴግ በህዳር 18 ላደረገው ስብሰባ ዋና መነሻ እና ግፊት የፈጠረበት)፡ በኢትዮጵያ አንድነት ሬድዮ ከስቶኮልም ስዊድን እንዲሁም በአሜሪካን ድምጽ ስትሬት ቶክ አፍሪካ (Straight Talk Africa) እና አፍሪካ 54 (Africa 54) የቀረበውን እና የአማርኛው ስርጭቱ በጁን 22, 2018, የተላለፈውን ሊንክ ደግመን እዚህ ላይ ልናስቀምጥ እንወዳለን። በተጨማሪም በዚህ ወር (December 5, 2018 The Political Parties Role In Africa) በሚል ያቀረበውን ዝግጅቱን እና ያየያዝናቸውን መረጃዎች እንዲመለከቱ በትህትና እንጠይቃለን።

ከዚህ በታች በስብሰባው ላይ በእርሶ በኩል ከተሰጡት መልሶች እና እንደ አጀንዳ ካቀረቧቸው ሃሳቦች በመነሳት ማለትም ፡ የኢሃደግ ሕገ መንግስት በደነገገው መሰረት እንደሆነ ምርጫ የሚካሄደው ፡ ከምርጫ በፊት ሳይሆን ከምርጫ በኋላ ሕገ መንግስቱ ላይ መነጋገር እንደሚቻል ፡ የተወሰነ ተቃዋሚ ከገባ እና ወራት ካስቆጠረ በኋላ ፡ የውጪ ዜግነት ይዛችሁ ለውድድር መሳተፍ አትችሉም ባሉት ላይ (ሁለት ዜግነት የኢሃደግ ሕገ መንግስት ስለማይፈቅድ ) ፡ ጉዳዩ በጣም አሳሳቢ በመሆኑ፡ ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቧ ከሚጠቅመው ሃሳብ ብቻ በመነሳት ከምርጫው በፊት በቅድሚያ በተግባር ሊሰሩ የሚገባቸውን ባጭሩ ከዚህ በታች እንዳለው ልናቀርብ እንወዳለን።

የሰው ልጅ ፡ ካንድ አፍሪካ እናት እና አባት የመጣባት ብቸኛዋ ጥንታዊት ታላቅ አገር ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ እንድትቀጥል ፡ በተረጋጋ መንፈስ ፡ መወያየት ፡ እጅግ አስፈላጊ እና ቀዳሚ ጉዳይ ነው። መጀመርያ አይን ለአይን እንደ ኢትዮጵያዊ መታየየት መቻል አለብን። ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን። እንደ እህል ዘር የተለያየን ሳንሆን ፡ መገኛችን ክብር እና ሞገሳችን ፡ ከአንዲት ኢትዮጵያ የሆንን የሰው ዘር ነን ብሎ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ስደት መንግስት ያምናል።

ዛሬ ፡ አሁን የተገኘ የለውጥ ድል ፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ መራራ መስዋእትነት የተገኘው ለውጥ በአገር ቤት እና በውጪው አለም በተለይም በአሜሪካን አገር ከምርጫ 97 በፊት ጀምረን ስንታገል በነበርነው የፓለቲካ ድርጅቶች ነው። ለኢትዮጵያ አንድነት ፡ ለሕዝቧ ሰላም፡ ለአሁንም ይሁን ለመጭው ትውልድ ሚዛናዊ እንዲሆን በማሰብ ቅደም ተከተል በማውጣት ፡ በእምነት እራሳችንን ሆነን ፡ በቅንነት ለኢትዮጵያ መልካም እና ዘላቂ የፍትህ አስተዳደር እንዲኖረን ጠልቀን መወያየት ስላለብን "ሳይቸኮል በሕገ መንግስት ነጻ ፍርደቤት ቢደነገግ" ምክኒያቱም ፡ ነጻ ፍርድ ቤት ሳይኖር ፡ የሕግ የበላይነት እክል ውስጥ ስለሚወድቅ ቢደመረም ቢቀነስም ፡ ማንም ምንም ማድረግ አይችልም እና በሕገ መንግስት ነጻ ፍርድ ቤት ፡ እንዲደነገግ እና የነጻው ፍርድ ቤት፡ የምርጫ ቦርዱን እንዲመሰርት ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት ባአጽንዖት ይጠይቃል። እስካሁን ፡ በለውጡ ኃይሎች የተደረጉትን ትንፋሽ ሰጪ እንቅስቃሴዎች በመደገፍ ጭምር ነው።

ለአንድ ችግር ፡ ጊዜያዊ መፍትሄ መስጠት ብቻ አቅም እና ጊዜን ያቀጭጫል። አብነቶቻችን እንዳሉት "አለባብሶ ቢያርሱት በአረም ይመለሱ" ይሆናል እና ችግሩን እስከወዳኛው ለማስወገድ ፡ ባስቀመጥነው ነጥብ ቢሰራ ብልህነት እና ኪሳራ የለሽ ይሆናል። እስካሁን በለውጡ ኃይሎች የተደረጉት ትግሎች እሰየው የሚያሰኙ ቢሆንም ፡ ችግሩን ከመሰረቱ ፈንቅሎ ለመጣል ፡ ከላይ የጠቀስነው የጎላ ነገር መሰራት ይኖርበታ ብለን እናምናለን። በጊዜው ልንጠቀምብት ይገባል ። መፈራራቱ ለብዙ መስዋእትነት እና ለኪሳራ ይዳርግል ብሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት ያምናል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር! ኢትዮጵያን እና ሕዝቧን እግዚአብሄር ይባርክ።

በታላቅ አክብሮት
የሐረር ወርቅ (የኢትዮጵያ ወርቅ) ጋሻው።
የኢትዮጵ ብሔራዊ የስደት መንግስት መስራች እና ፕሬዘደንት

P.S.
የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት : ከዲሴምበር 24,2018 እ.አ.አ.ጀምሮ ስሙን ወደ "የኢትዮጵያ ሴቶች ዲሞክራትክ ፓርቲ" እንደሚለውጥ ከወዲሁ ያስታውቃል።

ከዚህ በታች ስማቸውን ያስቀመጥነው በድርጅታችን አማካኝነት ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካን አገር ዳላስ ቴክሳስ ከኮሎኔል ጎሹ ወልዴ በስተቀረ ፡ በተለያየ ጊዜ ጋብዘን በማምጣት የፓለቲካ ፓርቲ ድርጅቶቻቸውን ፕሮግራም በአሜሪካን አገር ለሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ከሕዝቡም ጋር እንዲማከሩ እና አስፈላጊውን እርዳታ ሁሉ ሕዝቡ በራሱ ጊዜ በቀጥታ ወደ አገር ቤት እንዲልክላቸው ጭምር በማስተባበር እንኣቸው በጊዜው ለቆምነው ወገኖቻችን የዚችን ደብዳቤ ግልባጭ ይድረሳችሁ እንላለን።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ።
ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ።
ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ። በዋሽንግተን ዲሲ ኗሪ።
ዶክተር ኃይሉ አራያ።
ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና።
ዶክተር አድማሱ ገበየሁ። አሁን በአውሮፓ የሚኖሩ።
አቶ ልደቱ አያሌው።
አቶ መሃሙዳ ገሃስ።

Links:
Africa 54,TV VOA with Yeharerwerk Gashaw TPLF is about to dismantle Ethiopian Unity

**Yeharerwerk Gashaw, said “There is no fundamental change in Ethiopia” on VOA TV Straight Talk Africa 11,5,2018**

**Stright Talk Africa VOA TV with Yeharerwerk Gashaw on Jan. 10,2018 https://www.voanews.com/a/4202019.html**

1. https://welkait.com/?p=18279

2. Letter from Herman Cohen to Yeharerwerk Gashaw.
https://welkait.com/?p=11316

Ethiopian National Government In Exile with SBS Radio 11,12,2018

3. https://www.sbs.com.au/yourlanguage/amharic/en/audiotrack/ethiopian-national-government-exile-yeharerwerk-gashaw
4. To meet with Pres. Obama
5. http://ethiopatriots.com/pdf/sedetMengest150706.pdf

   Legal Certificate of Ethiopian National Government In Exile

6. http://ethiopatriots.com/pdf/Ethiopian%20National%20Government%20In%20Exile%20certificate150719.PDF

7. http://ethiopatriots.com/EthioAR/Ethiopia-Andnet-YEAHREWORK-GSHAW%20interview20151122-1700.mp3

8. For Ethiopian POW release in 1999 with the help of Yeharerwerk Gashaw , And Nelson Mandela , Yeharerwerk , Marshal Mobutu and with African leaders. https://www.youtube.com/channel/UC3uWFAaLITiEmKO8NQSTjmA